# ሥነ ፍጥረት



እግዚአብሔር ፍጥረታትን የፈጠረው ሰውንና መላእክትን ስሙን ለመቀደስ ክብሩን ለመውረስ ሲሆን የተቀሩትን ፍጥረታት ግን ለአንክሮ ለተዘክሮ ለምግበ ስጋ ለምግበ ነፍስ ነው። /መዝ.148፣1-3 ራዕ4፣11 የሐ.ሥራ14፣17 ሮሜ.1፣20/እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ ፈጥሮ ያከናወነው በስድስት ቀናት ውስጥ ነው፡፡ /ዘፍ2 እና ዘጸ.20፣9-11/ በእነዚህ ቀናት የተፈጠሩት ፍጥረታት እያንዳንዳቸው ቢቆጠሩ ፍጡር ተናግሮ አይፈጽመውም ነበር፡፡ ነገር ግን በባሕርያቸው በአኗኗራቸው በ22 ይመደባሉ፡፡( ኩፋሌ 3፣9 )

## ፍጥረታት የተገኙበት ሁኔታ በሁለት ሁኔታ ነው፡፡

እነርሱም

1 እምኀኀበ አልቦ ኀበ ቦ (ካለመኖር ወደመኖር) በማምጣት ሲሆን

እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ (ካለመኖር ወደ መኖር) በማምጣት የፈጠራቸው ፍጥረታት አራቱ ባሕርያት ማለትም ነፋስ ፣ እሳት ፣ውሃና መሬት ፣ ጨለማና መላእክት ናቸው፡፡

2 ሁለተኛው ደግሞ ግብር እም ግብር ከተፈጠሩት ላይ በመፍጠር ነው፡፡

ግብር እም ግብር (ከተፈጠሩት ላይ በመፍጠር) የተፈጠሩት ደግሞ ሌሎቹ ፍጥረታት ናቸው፡፡ መገኛቸውም አራቱ ባሕርያተ ስጋ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር አምላክ እነሱን በማዋሐድ ፈጥሯቸዋል፡፡

## ፍጥረታት የተገኙበት መንገድ ደግሞ ሦስት ናቸው፡፡

እነርሱም፡-

በዝምታ /በአርምሞ/፡- አራቱ ባሕሪያተ ስጋ፣ ጨለማ፣ መላእክት፣ ሰማያት

በመናገር /በነቢብ/፡- ብርሃን፣ የዕለተ ሰኞ፣ የዕለተ ማክሰኞ፣ የዕለተ ረቡእ እና ሐሙስ ሥነ-ፍጥረታት ናቸው፡፡

በመስራት /በገቢር/ ፡ -ሰውን ብቻ፡፡

**፩ እሁድ** ማለት አሀደ አንድ መጀመሪያ ማለት ነው፡፡ እሑድ የተፈጠሩት ፍጥረታት ስምንት ናቸው ፡፡

1 ጨለማ 3 ውሃ 5 ነፋስ (አየር) 7 መላእክት

2 መሬት 4 እሳት 6 ሰባቱ ሰማያት 8 ብርሃን (8)

**፪ ሰኑይ** (ሰነየ አማረ ፤ በጀ ፤ ተስተካከለ) ፤ ካለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ቃል ሲሆን እግዚአብሔር በዚህ ቀን የፈጠረው አንድ ፍጥረት <u>ጠፈርን (ሰማይ)</u> ብቻ ነው ። ከመሬት (አፈር) ጋር ተዋህዶ የነበረውን ውሃ <u>ከሶስት ከከፈለ</u> በኋላ አንደኛውን ባለበት እንዲረጋ አድርጎ፤ ጠፈር *(ሰማይ)* አለው ፤ ሁለተኛውን ከመሬት ጋር እንደተቀላቀለ (ድፍርስ እንደሆነ) ከጠፈር በላይ አደረገው ስሙም ሐኖስ ይባላል ። ዘፍ 1 ፡ 6 ። ሶተኛውንም ከውሃ ጋር እንደተቀላቀለ ከጠፈር በታች ተወው ። (1)

**፫ ሰሉስ** (ማክሰኞ) ሦስት ፍጥረታትን ፈጠረ፡

በእጅ የሚለቀሙ አትክልት (በመሬት ውስጥ የሚያፈሩ እንደ ካሮት ድንች ...)

በማጭድ የሚታጨዱ አዝርዕት (የአገዳ እህሎች እንደ ገብስ ስንዴ በቆሎ ጤፍ ...)

በመጥረቢያ የሚቆረጡ ዕፀዋት (የዛፍ ዓይነቶች እንደ ዋርካ ወይራ ሾላ...) የመሳሰሉት ናቸው ። (3)

<u>**፬ ረቡዕ**</u> “ረብዐ አራት አደረገ“ በእለተ ረቡዕ ሦስት ፍጥረታትን ፈጠረ፡፡

<u>ፀሀይን</u> ፈጥሮ ከእሳት ብርሃኑንና ሙቀቱን ከሳለበት በኋላ በቀን እንዲያበራ ሾመው።

<u>ጨረቃን</u> ሰሌዳውን አዘጋጅቶ በፀሀይ ብርሃን ነፀብራቅ በሌሊት እንዲያበራ አደረገው ።

<u>ከዋክብትን</u> በተለያየ መጠን ካዘጋጀቸው በኋላ ብርሃን ስሎባቸው በሌሊት እንዲያበሩ ሾማቸው ። (3)



**፭ ሐሙስ** ፤ ሐመሰ አምስት አደረገ ካለው ቃል የተገኘ ሲሆን ፤ ለፍጥረት አምስተኛ ቀን ነው ።

በዚህ ቀን እግዚአብሔር ከባህር በደመ ነፍስ ህያዋን ሆነው የሚኖሩ ፤ <u>ሶስት</u> ተንቀሳቃሽ ፍጥረታትን ፈጠረ ። ዘፍ1፥20፡23 በእለተ ሐሙስ ሦስት ፍጥረታትን ፈጠረ

(3)

እነዚህም በልብ የሚሳቡ እንስሳትና አራዊት ( ዘመደ እንስሳ፡-አሳዎች)

በእግር የሚሽከረከሩ እንስሳትና አራዊት ( ዘመደ አራዊት፡- አዞ)

በክንፍ የሚበሩ አእዋፍ ናቸው ። ( ዘመደ አእዋፋት፡- ዳክዬዎች)

**፮ ዐርብ** ፣ዐረበ ፣ገባ ፤ ተካተተ ፤ ካለው የወጣ ሲሆን ፤ መካተቻ ማለት ነው ፤ ለፍጥረት ስድስተኛ ቀን ነው ።

እግዚአብሔር በዚህ ቀን በመጀመሪያ ከየብስ በደመ ነፍስ ህያዋን ሆነው የሚኖሩ <u>ሶስት</u> ተንቀሳቃሽ ፍጥረታትን ፈጠረ ። ዘፍ 1 ፡24 ።በዚህ ቀን እግዚአብሔር አራት ፍጥረታትን ፈጠረ፡፡

በልብ የሚሳቡ እንስሳትና አራዊት

በእግር የሚሽከረከሩ እንስሳትና አራዊት

በክንፍ የሚበሩ አእዋፍ ናቸው (3)

(እንስሳት፡አራዊት አዕዋፋት)

በመጨረሻም እግዚአብሔር “ ሰውን በመልካችንና እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር ” ብሎ ከሰባቱ ባህርያት ፈጠረው ። ሰባት ባህርያት የሚባሉት <u>አራቱ</u> ባህርያተ ሥጋ(መሬት : ውሃ: እሳት : ነፋስ) ሲሆኑ <u>ሶስቱ</u> ባህርያተ ነፍስ የሚባሉት ደግሞ ልብ (ማሰብ) ቃል (መናገር) እስትንፋስ (በሕይወት መኖር) ናቸው ። ዘፍ 1 ፥26 (1)

22ቱ ሥነ-ፍጥረት የሚባሉት እነዚህ ከላይ ያየናቸው ናቸው፡፡

**፯ ቅዳሜ** በሰባተኛው ቀን ቅዳሜ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ ፈጥሮ ከስራው አረፈ፡፡ ስለዚህ ይህች ዕለት ሰንበት ሆና እንድትከበር ሥጋዊ ስራዎች እነዳይሰሩባት የእግዚአብሔር መልካም ፍቃድ ሆነ፡፡ ይኸውም እግዚአብሔር ከስራው ሁሉ አርፎባታልና ነው /ዘፍ.2፣2/፡፡

## ፨ አዳምና ሄዋን (ክፍል1)

አዳም ማለት ከመሬት የተፈጠረ ያማረ፣ መልከ መልካም ማለት ነው ሲሆን የተፈጠረውም ከአራቱ ባሕሪያተ ሥጋ (ማለትም ከነፋሰ፤ ከእሳት፤ ከውኃ፤ ከመሬት፤) እንዲሁም ከሦስቱ ባሕሪያተ ነፍስ (ማለትም ከልብ: ከቃል: ከስትንፋስ) በመጀመሪያ ሱባኤ ነው፡፡ የሥነ ፍጥረት መካተቻ በሆነች በዕለተ ዓርብ በ 3 ሰዓት ከህቱም ምደር በሚያዝያ 4 ቀን በምድር መካከል በምትገኝ ኤልዳ በተባለች ስፍራ በነግህ የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ ሆኖ በእግዚአብሔር አርአያና መልክ ተፈጠረ፡፡ ዘፍ 1÷27 ፤ ኩፋሌ 5÷ አዳም ለእንስሳት፣ ለሰማይ ወፎች እና ለምድር አራዊት ሁሉ ተባዕትና አንስት ሆነው ሲመጡ ስም ያወጣላቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ለአዳም እንደ እራሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር፡፡ፈጽሞ ሳይተኛ ፈጽሞ ሳይነቃ ከጎኑ አጥንት አንስቶ ያቺን ሥጋ አልብሶ የ15 ዓመት ቆንጆ አድርጎ ፈጠራት፡፡ (ዘፍ 2፥18) አዳምም ስሟንም ሔዋን አላት ሔዋን ማለት ‹ሐይወ› ካለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም የሕያዋን ሁሉ እናት ማለት ነው፡፡አዳምና ሔዋንን እስከ 40 ቀን ድረስ በተፈጠሩበት በማዕከለ ምድር በቀራንዮ አሰነበታቸው፡፡ ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰቀልበትን ቦታ ነውና፡፡ ከዛም በ40ኛው ቀን አዳምን ብርሃን አልብሰው ብርሃን አጎናጽፈው የብርሃን ዘውድ አቀናጅተውት በብርሃን ሰረግላ አስቀምጠውት ወደ ገነት አስገቡት፡፡ ሔዋንንም በ80 ቀኗ እንደ አዳም ባለ ክብር ወደ ገነት አስገቧት፡፡(ኩፋ 4፥12-15) አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር የባሕርይ ደግነት የተነሳ እርሱን ለማመስገንና ክብሩን ለመውረስ ተፈጠሩ፡፡ ኩፋሌ 4÷3-5

# ፨ አዳምና ሄዋን (ክፍል2)



አዳምና ሄዋን በገነት እራቁታቸውን ሳሉ /ሲኖሩ/ አይተፋፈሩም ነበር።አዳምና ሄዋን በገነት ውስጥ ሳሉ ሁሉንም ፍሬ የመብላት ፥ እንስሳቱን የማዘዝ ፥ የመግዛት፥ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል ።
እግዚአብሔርም በገነት መካከል መልካሙንና ክፉውን የሚያስታውቀው እና እንዲሁም የህይወት ዛፍ አበቀለ ። ነገር ግን እፀ በለስን (መልካሙንና ክፉውን)እንዳይበሉ እግዚአብሔር አዟቸዋል ። በበላችሁም ጊዜ ትሞታላችሁ አላቸው።
በገነት ውስጥ ሶስት ዓይነት ዛፎች ነበሩ፡

ሀ.ዕፀ መብል፡- እንዲበሉት የተፈቀደላቸው ምግብ ነው፡

ለ. ዕፀ በለስ፡- እንዳይበሉት የታዘዙት ነው፡፡

ሐ. ዕፀ ሕይወት፡- እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ቢመገቡት የዘላለም ሕይወት የሚሠጥ ምግብ ነው፡፡ ነገር ግን ብሉም አትብሉም አላላቸውም ዲያብሎስ በእባብ አድሮ ሄዋንን እንዲህ ብሎ አሳሳታት :- እግዚአብሔር እጸበለሰ አትብሉ ያላችሁ እኮ እጸበለሱን ከበላችሁ አይነ ልቦናችሁ እንዳይገለጽ ።እንደ እግዚአብሔር የባሕርይ አምላክ እንዳትሆኑ።ክፉውንና መልክሙን እንዳታውቁ ስለፈለገ ነው እንጂ አትሞቱም እላት።ሄዋንም እጸ በለሱ ሊበሉት የሚያስጎመዥ ፥ ሲያዩት ደስ የሚያሰኝ በጎውን ነገር የሚያሳውቅ መሆኑን ባየች ጊዜ ለአዳም ሰጠችው አብረውም በሉ።

## ፨ እጸ በለሱን ከበሉ በኋላ:-

ዓይነ ልቦናቸው ተገለጠ ዓይናቸውም አየ።
አራቁታቸውን መሆናቸውን አወቁ ።ዲያቢሎስ በበጎ አስመስሎ /እንደ ወዳጅ ሆኖ / ነግሯቸው ስለነበር ክፉ ሆኖባቸዋል።አፍረው የበለስ ቅጠል ሰፍተው ለበሱ ። ከእግዚአብሔር ፊት በገነት ዛፍ መካከል ተደበቁ /ተሰወሩ/።እግዚአብሔር አምላክ አዳምን አትብላ ካልኩህ ዛፍ በላህን ? ብሎ ጠየቀው
አዎ ከኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ፍሬ ሰጠችኝ በላሁ አለ።

እግዚአብሔር ሔዋንን ይህንን ያደረግሽው ለምንድነው ? አላት ።

ሔዋንም እባብ እሳተችኝና በላሁ አለች ።አዳምና ሔዋን ከገነትም ተባረሩ። ወደ ሕይወት ዛፍ(ዕፀ ሕይወት) የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በዔድን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ (አዳምና ሔዋን ይህን ሕግ በማክበር በገነት ውስጥ ለ7 ዓመት ከ2 ወር ከ17 ቀን ኖሩ፡፡)
ተባርከው የነበሩ ተረገሙ።ተሰጥተው የነበሩ ተቀሙ።ተከብረው የነበሩ ተዋረዱ ።
ለብሰው የነበሩ ተራቆቱ ።ሕይወታቸውን በሞት ለወጡ

## ፨እርግማን ፥ቅጣት፥ ብይን።


እግዚአብሕር አዳምና ሄዋንን ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ውጭ ስለሆኑ እንዲህ ብሎ ረገማቸው
ሔዋንን፡- በፀነስሽ ጊዜ ጭነቅተሽነ እጅግ አበዛዋለሁ በጭንቅ ትወልጃለሽ አላት።
አዳምን:- ከመሬት ተፍጥረሃልና ወደ መሬት ትመለሳለህ ስትሞትም ነፍስህ ሲዖል ትወርድና በሰይጣን ተሰቃይ እንዲሁም ለፍተህ ጥረህ ግረህ ብላ አለው።
እባብን:-ድሮ እባብ ስትፈጠር እንደ ግመል ዐራት እግር ነበራት ። አንስሳት ሁሉ አዳም ስም እንዲያወጣላቸው ወደ ገነት ሲጓዙ እባብን ዲቢሎስም ከገነት ውጭ መንገድ ላይ አግኝቷት አዳምን ሊያሳስት አታሏት ወደ ገነት አዝላው እንትገባ አደረጋት ።ከዚያም በእባብ አደረ አዳምና ሄዋንን ዲያብሎስ አሳታቸው።እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ እባብን ረገማት ። ልጇ አዳም ባንቺ የተነሳ ስለትሳሳተ ዲያብሎስን ያመጣሽበት እግሮችሽ በሆድሽ ይግቡ በልብሽም ተስበሽ ኑሪ ብሎ ረገማት (ዘፍ3፥14)

እግዚአብሔር አዳም የት ነህ ? እያለ የሚፈልግህ ፥ ሊገርፍህ ወይም ሊቀጣህ ወይንም ሊቆጣህ አይደለም ፤ ወደ ቤት እንዲመልስህ እንጂ ፤ እንዲያጽናናህ እንጂ ፥ እንዲያበረታህ እንጂ ፥ እንዲምርህ እንጂ ፥ አቅፎና ደግፎ እንባህን ጠርጎ ወደሬሱ ሊመልስህ እንጂ ። በሥላሴ ስም የተጠመቅህ ክርስቲያን ሆይ የት እንዳለህ ለአባትህ መንገር አትፍራ ። የትም ሁን የት ያለህበትን ንገረው ።



## ፨ቃል ኪዳን

አዳምና ሔዋን በሰሩት ኃጢአት በመፀፀታቸውና በንስሐ በመመለሳቸው እግዚአብሔር አምላክ ለአዳም 5 ቀን ተኩል ወይም 5500 ዘመን ሲፈፀም ሰው ሆኖ በመወለድ እንደሚያድናቸው ቃልኪዳን ገባላቸው ዘፍ 3÷15-22 ምንም እንኳን አዳም ቢበድል እና ከገነት ቢባረርም ስለበደለው በደል ንስሐ በመግባቱ ወይንም ስለተጸጸተ እግዚአብሔር ደስ ብሎት ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመት በኋላ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ እንደሚያድነው ነገረው።





1 እግዚአብሔር አዳምን በስንተኛው ቀን /ፈጠረው/ ሠራው ?

..........................................................................................................

2 እግዚአብሔር አዳም እንዴት/ከምን/ ሠራው ?

..........................................................................................................

3 አዳም የተፈጠረው ከሳምንቱ በየትኛው ቀን ነው?

..........................................................................................................

4 አዳም ማለት ምን ማለት ነው ?

..........................................................................................................

5 አዳም ገነት ሲገባ ስንት ዓመቱ ነበር?

..........................................................................................................

6 እግዚአብሔር አዳምን ወደ ገነት ያስገባው በስንት ቀኑ ነው ?

..........................................................................................................

7 ሄዋን ማለት ምን ማለት ነው ?

..........................................................................................................

8 እግዚአብሔር ሄዋንን እንዴት/ከምን/ ፈጠራት ?

..........................................................................................................

9 እግዚአብሔር ሄዋንን ወደ ገነት ያስገባት በስንት ቀኗ ነው?

..........................................................................................................

10 ሄዋን ስትፈጠር የስንት ዓመት እድሜ ነበራት?

..........................................................................................................

ሰም --------------------------------

ቀን ----------------------------

1 በገነት ሳሉ የእንሰሳቱ ሁሉ አለቃ ማን ነበር ?

..........................................................................................................

2 እግዚአብሔር በገነት ውስጥ ሳሉ ለአዳምና ለሄዋንን ምን ትዕዛዝ ሰጣቸው?

.....................................................................................

3 እጸ በለስ የት ነበር የበቀለችው ?

.....................................................................................

4 እጸ በለስ ምን ማለት ነው ?

.....................................................................................

5 አዳምና ሄዋን እጸ በለስ ከበሉ በኋላ ምን ሆኑ ?

.....................................................................................

.....................................................................................

6 እባብ ስንት እግር ነበራት ?

.....................................................................................

7 እግዚአብሔር ሔዋንን ምን ብሎ ረገማት?

.....................................................................................

8 እግዚአብሔር አዳምን ምን ብሎ ረገመው?

.....................................................................................

9 እባብን ምን ብሎ ረገማት ?


.....................................................................................

10 አዳምና ሄዋን ከገነተ ከተባረሩ በኋላ እግዚአብሔር ምን ቃል ኪዳን ገባላቸው?




# አቤልና ቃየል

አቤልና ቃየል የአዳምና ሄዋን ልጆች ናቸው የቃየል መንትያ ሉድ ፥የአቤል መንትያ አቅሌማ ይባላሉ ዘፍ 4፥1-17አቤል በግ ጠባቂ እረኛ ነበር ቃየል ደግሞ ምድርን የሚያርስ የሚቆፍር ገበሬ ነበር።ከብዙ ቀን በኋላም በትውፊት ከአባታቸው አዳም በተማሩት መሠረትለእግዚአብሔር መስዋዕት አቀረቡ።ቃየን ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን አቀረበአቤል አግዚአብሔር ቅዱስ ሰለሆነ ንጹህ እና ቆንጆ ነገር ስለሚፈልው የሚያምረውን ያላረጀውን ከበጎቹ በኵራትና ከስቡ አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ እግዚአብሔር የአቤልን መስዋዕት ተቀበለ።እግዚአብሔር ቃየንን እንዲህ „አለው መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚበራ አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅ ታደባለች ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው፥ አንተ ግን በእርስዋ ንገሥባት።“እግዚአብሔር ቃየልን እንዲህ አለው ልቦናህ ለምን አዘነ አለው ።አንገትህንስ ለምን ደፍተሃል የሚገባውን መስዋዕት በእውነት አላቀረብክምናዝም በል አለው ።ቃየንም ወንድሙን አቤልን፡- ና ወደ ሜዳ እንሂድ እህሉን ተክሉን ጎብኝተን እሸቱን እንኩቶውን በልተን ወኃ ጠጥተን እንምጣ አለው።በሜዳም ሳሉ ቃየን በወንድሙ በአቤል ላይ ተነሣበት፥ ገደለውም። እግዚአብሔርም ቃየንን አለው፡- ወንድምህ አቤል



ወዴት ነው? እርሱም አለ፡- አላውቅም የወንድሜ ጠባቂው እኔ ነኝን?

አለውም፡- ምን አደረግህ? የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል።አሁንም የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ።ምድርንም ባረስህ ጊዜ ፍሬውን አትሰጠህም፥ ተዘራለህ ምድር አታበቅልም፥ የተከልከውን ምድር እታጸድቅም ምድርም ላይ ኰብላይና ተቅበዝባዥ ትሆናለህ።





ስም --------------------

ቀን .........................

1 በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትክክል በጽሁፍ መልስ

ሀ/ አዳምና ሔዋን ስንት ልጆች ነበሯቸው ስማቸውን ጥቀስ

.....................................................................................

ለ/አቤልና ቃየለ ለእግዚአብሔር መስዋዕት ማቅረብን እንዴት ተማሩ

...........................................................................................................

2 በምንባቡ መሠረት ዳሹን ሙላ

ሀ/አቤል ሥራው........................................ ነበር

ለ/ቃየል ሥራው .........................................ነበር

3 በምንባቡ መሠረት አዛምድ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 0 | አዳም | ...ሸ..... | ሀ የአቤል ሥራ |
| 1 | ቃየል | ...... | ለ የቃየል ሥራ |
| 2 | አቤል | ....... | ሐ መስዋዕቱን እግዚአብሔር ተቀበለ |
| 3 | ሉድ | ......... | መ መስዋዕቱን እግዚአብሔር አልተቀበለም |
| 4 | አቄልማ | ...... | ሠ የአቤል መንትያ |
| 5 | እረኛ | ... ...... | ረ የቃል መንትያ |
| 6 | ገበሬ | ....... | ሸ ሔዋን |

4 አቤል ለእግዚአብሔር ምን ዓይነት መስዋዕት አቀረበ ?

.......................................................................................................

.......................................................................................................

5 ቃየል አቤልን ለምን የገደለው ይመስልሃል ?

.......................................................................................................

.......................................................................................................

6 የአቤልና የቃየል መስዋዕት እንዴት ይለያያል ?

የአቤል መስዋዕት ....................................................

የቃየል መስዋዕት...................................................................

7 እግዚአብሔር ቃየልን ወንድምህ ወዴት ነው ሲለው ምን ብሎ መለሰ ?

.....................................................................................

.....................................................................................

# ኖኅ

እግዚአብሔር አምላክ አዳምና ሔዋንን ፈጥሮ በምድር ላይ ከተዋቸው በኋላ
የሰው ልጅ በምድር ላይ መብዛት ጀመረ ።በዚህም መሠረት ኖህ ከአዳም ከሴት ልጅ 10ኛው (፪)
ትውልድ ሆኖ ተወለደ።
ኖህ ማለት ዕረፍት ትፍስሕት ተረፈ ማለት ነው። ከመገዛቴ ያሳርፈኛል በእጄ ሥርቼ በቃሌ ተናግሬ
ከመጣብኝ ኃዘን ደስ ያሰኘኛል እግዚአብሔር የረገማት ምድር ስትጠፋ እርሱ ይቀራል ሲል ኖኅ ብሎ ስም
አወጣለት ዘፍ 5፥29።
በኖኅ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች እግዚአብሔርን ትእዛዝ ትተው ሥራቸው
በኃጢአት እና በክፋት የተሞላ ሆነ ። ምድርም ከኃጢአት የተነሳ ረከሰች። እግዚአብሔርም
በክፋታቸው አዘነ ።እነርሱን በመፍጠሩ ተጸጸተ።
እግዚአብሔር በሠራው ሥራ የሚጸጸት ሆኖ ሳይሆን የእነርሱ ሥራ የሚያሳዝን
መሆኑን ሲያሳይ ነው። ነገር ግን ኖኅ ከዚህ ሁሉ ተለይቶ ፍጹምና ጻድቅ እንደ አያቱ እንደ ሄኖክ
አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ነበር ዘፍ 6፥9 ።

## እግዚአብሔር ለኖኅ ያዘዘው ትእዛዝ

እግዚአብሔር የጥፋት ውኃ በምድር ላይ እንደሚመጣ አስጠነቀቀው። ኖኅና ቤተሰቦቹ እንዲሁም ሕያው
ነፍስ ካላቸው ተባእትና(ወንድና) አንስት(ሴት) ፍጥረታት (ከሚበሉት ሰባት ሰባት ከማይበሉት ሁለት ሁለት)
የሚድኑበትን መርከብ እንዲያዘጋጅ ታዘዘ ዘፍ 6፥13-22።
መርከቡን እስኪያዘጋጅ እግዚአብሔር ታገሠ። ኖኅም ጽድቅን ያስተምር ነበር (፩ ) ።
(፩)

(፩) እግዚአብሔር በሰው ልጅ
እንዳዘነ ምድር በኃጢአት
እንደረከሰች ስለዚህም
እግዚአብሔር በውኃ ነፍስ
ያለውን ሁሉ እንደሚያጠፋ
ስለዚህ ሁሉም ወደ
እግዚአብሔር እንዲመለሱ ንስሐ
እንዲገቡ ያስተምር ነበር።
ነገር ግን ሰው ሁሉ ገና ጊዜ አለን
እንዝናና፥ እንጨፍር ፥እንዘሙት
ተወን እያሉ ኖኅን እልሰሙት
ነበር

(፪)
አዳም ደግሞ ሚስቱን አወቀ ወንድ
ልጅንም ወለደች። ስሙንም፡- ቃየን
በገደለው በአቤል ፋንታ እግዚአብሔር
ሌላ ዘር ተክቶልኛል ስትል ሴት
አለችው።
አዳምም ሴትን ወለደ
ሴትም ሄኖስን ወለደ
ሄኖስም ቃይናንን ወለደ፤
ቃይናንንም መላልኤልን ወለደ
መላልኤልም ያሬድን ከወለደ
ያሬድም ሄኖክን ከወለደ
ሄኖክም ማቱሳላን ወለደ፤
ማቱሳላም ላሜሕን ወለደ
ላሜሕም ኖኅን ከወለደ



# *ኖኅና መርከቡ*

ኖኅ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ።ኖኅም ሦስት ልጆችን ሴምን
ካምን
ያፌትንም ወለደ።ምድርም በእግዚአብሔር ፊት ተበላሸች፤ ምድርም ግፍን ተሞላች።
እግዚአብሔርም ምድርን አየ፥ እነሆም
ተበላሸች፤ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በምድር
ላይ መንገዱን አበላሽቶ ነበርና።




*እግዚአብሔርም ኖኅን አለው።ከጎፈር*
*እንጨት መርከብን ለአንተ ሥራ፤*
*የመርከቢቱንም በር በጎንዋ አድርግ፤*
*ታችኛውንም ሁለተኛውንም*
*ሦስተኛውንም ደርብ ታደርግላታለህ።*

እግዚአብሔር ለኖህ ቤትሰቦችና ለዘር የሚሆኑ እንስሳት ወንድና ሴት እያደረገ
ወደ መርከቡ እንዲያስገባ አዘዘው።ኖኅም ልጆቹ ሴም ካም ያፌትና የኖኅ ሚስት
ሦስቱም የልጆቹ ሚስቶች ከእርሱ ጋት ገቡ።ሥጋ ካለው ሁሉ ወንድና ሴት
እግዚአብሔር እንዳዘዘው *ገቡ።* እግዚአብሔርም ከበስተኋላ ዘጋበት።

ኖህም ልክ 600 ዓመት ሲሆነው ከሰማይ ታላቅ የጥፋት ውኃ መዝነብ ጀመረ
ሳያቋርጥ ፵ ቀናን ፵ ሌሊት ወረደ ።ውኃም ታላላቅ ተራሮችን ሸፈነ ኖኅና ከእርሱ
ጋር ወደ መርከብ ከገቡት በስተቀር የዳነ አልነበረመ( ዘፍ 7፥1-ፍ ) በየብስ የነበረው
በአፍንጫው የሕይወት እስትንፋስ ያለው ሁሉ ሞተ። ኖኅም አብረውት በመርከብ
ከነበሩት ጋር ብቻውን ቀረ።ውኃውም መቶ አምሳ (150) ቀን በምድር ላይ ሸፈነ።

ቁራንም ውኃው ከምድር ፊት ቀልሎ እንደ ሆነ ለማወቅ ሰደደው ፤ እርሱም
ወጣ፤ ውኃው ከምድር ላይ እስኪደርቅ ድረስ ወዲያና ወዲህ ይበር ነበር።ርግብንም
ውኃው ከምድር ፊት ቀልሎ እንደ ሆነ እንድታይ ከእርሱ ዘንድ ሰደዳት (ላካት)።
ነገር ግን ርግብ እግርዋን የምታሳርፍበት ስፍራ አላገኘችም፥ ወደ እርሱም ወደ ኖኅ መርከብ
ተመለሰች፥ውኃ በምድር ላይ ሁሉ እንዳልደረቀ አስታወቀችው። ።

ከዚያም በኋላ ደግሞ *ከሰባት ቀን በኋላ፤* ርግብንም እንደ ገና ከመርከብ
ሰደደ(ላካት)።ርግብም በማታ ጊዜ
ወደ እርሱ ተመለሰች፤ በአፍዋም
እነሆ የለመለመ የወይራ ቅጠል ይዛ
ነበር። ኖኅም ከምድር ላይ ውኃ እንደ
ቀለለ አወቀ። ውኃውም ደረቀ።



እግዚአብሔርም ኖኅ
ቤተሰቡና እንስሳቱ በሙሉ
ከመርከቡ እንዲወጡና

በምድር ላይ እኒዲራቡ (እንዲባዙ ) ነገረው። ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠዊያውን ሠራ
ከንጹሓን ወፎች ሁሉ ወስዶ መሥዋዕት አቀረበ። ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠዊያውን
ሠራ ከንጹሓን ወፎች ሁሉ ወስዶ መሥዋዕት አቀረበ። እግዚአብሔርም ኖኅና ቤተሰቦቹን ባረካቸው እንዲህም አላቸው ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት እኔም ቃልኪዳኔን ከእናንተና በኋላ ከሚመጣው ከዘራችሁ ጋር አቆማለሁ ሥጋ ያለው ሁሉ ዳግመኛ በጥፋት ወኃ አይጠፋም።

እግዚአብሔር በእኔና በናንተ መካከል ከእናንተም ጋር ባለው በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል ለዘላለም የማደርገው የቃልኪዳኑም ቀስቴን በደመና አድርጌያለሁ የቃልኪዳኑም ምልክት በኔና በምድር መካከል ይሆናል።በምድር ላይ ደመናን በጋረድሁ ጊዜ ቀስተደመና ትታያለች ቃልኪዳኔንንም አስባለሁ ሥጋ ያለውንም ሁሉ ያጠፋ ዘንድ ዳግመኛ የጥፋት ወኃ አይሆንም ።



ለልጆችህም ኣስተምሪው በቤትህም ፥ ስትቀመጥ ፥ በመንገድም ስትሄድ፥ስትተኛም፥ስትነሳም ተጫወተው

ዘሁልቁ 6፥7



ይህንን ጥያቄ ስትሠራ በተቻለ መጠን እራስህ ጻፍ ሌላ ሰው ማጻፍ ጥሩ አይደለም። በምንባቡ መሠረት ሙሉ መልስ

ስም ---------------------
ቀን .........................

## የሚከተሉት ጥያቄውዎች በምንባቡ መሠረት መልስ (አብራራ)

1 እግዚአብሔር ለምን ፈጥረቱን ሁሉ በውኃ ሊያጠፋ ፈለገ ?

....................................................

2 ኖኅ የሠራው መርከብ ውስጥ እንስሳት ለምን ይገባሉ ?

....................................................

3 በኖኅ መርከብ ውስጥ ስንት ሰው ዳነ?

....................................................

4 የኖኅን መርከብ ከበስተኋላ የዝጋው ማነው ?

....................................................

5 የጥፋት ውኃ መዝነብ የጀመረው መቼ ነበረ?

....................................................

6 የጥፋት ውኃ ለምን ያክል ጊዜ ዘነበ?

....................................................

7 ከጥፋት ውኃ በኋላ በምድር ላይ ድኖ (ሳይሞት) የተገኘ ማነው?

....................................................

8 ውኃው ለስንት ቀን ያህል ምድርን ሸፍኖ ነበር ?

....................................................

9 ኖኅ ውኃ በምድር ላይ መጉደሉን ለማወቅ ምን አደረገ?

....................................................

10 ኖኅ ውኃ ከምድር ላይ መድረቁን እንዴት አወቀ ?

....................................................

11 ኖኅ ለእግዚአብሔር መስዋዕት ምን አቀረበ ?

....................................................

12 እግዚአብሔርስ ኖኅን ምን ሎ መረቀው ?

....................................................

13 በእግዚአብሔር እና በምድ ላይ ባሉ በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል ያለው ቃል ኪዳን ምድነው ?

....................................................

14 ኖኅ ስንት ልጆች ነበሩት ስማቸውን ጻፍ ?

....................................................

15 የኖኅ መርከብ ስንት ደርብ (ፎቅ) ነበራት ?

....................................................

# አብርሐም /ክፍል 1/

የታራም ትውልድ እነሆ ይህ ነው። ታራ አብራምንና ናኮርን ሐራንንም ወለደ፤ ሐራንም ሎጥን ወለደ።ታራም የአብርሃም አባት ቤተሰቡ ሁሉ  እግዚአብሔርን የማያውቁ በጣዖት የሚያምኑ ነበር።ታራም ጣዖትም  እየሸጠ ይተዳደር ነበር። አብራም ግን በልቡ እግዚአብሔርን ፈልጎ አገኘ።

እግዚአብሔርም አብራምን አለው። ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ። አብራምም ሚስቱን ሦራንና የወንድሙን ልጅ ሎጥን፥ ያገኙትን ከብት ሁሉና በካራን ያገኙአቸውን ሰዎች ይዞ ከካራን  ወደ ከነዓን ምድር ለመሄድ ወጣ፤ ወደ ከነዓንም ምድር ገቡ።እግዚአብሔርም ለአብራም ተገለጠለትና። ይህችን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ አለው። እርሱም ለተገለጠለት ለእግዚአብሔር በዚያ ስፍራ መሠውያን ሠራ።አብራምም ከዚያ ተነሣ፥ እየተጓዘም ወደ አዜብ ሄደ።



አብራምም ድንኳኑን ነቀለ መጥቶም በኬብሮን ባለው በመምሬ የአድባር ዛፍ ተቀመጠ፤ በዚያም ለእግዚአብሔር መሠውያን ሠራ።ይህችን ምድር ትወርሳት ዘንድ እንድሰጥህ ከከለዳውያን ዑር  ያወጣሁህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ አለው።ዘፍ15፥6

አብራምም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሰው በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ለአብራም ተገለጠለትና። ለብዙ አሕዛብም አባት ትሆናለህ።ከዛሬም ጀምሮ እንግዲህ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ፥ ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል፤ ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና። እጅግም አበዛሃለሁ፥ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ ነገሥታትም ከአንተ ይወጣሉ።በእንግድነት የምትኖርባትን ምድር፥ የከነዓን ምድር ሁሉ፥ ለዘላለም ግዛት ይሆንህ ዘንድ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ፤ አምላክም እሆናቸዋለሁ።  እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው። የሚስትህን የሦራን ስም ሦራ ብለህ አትጥራ፥ ስምዋ ሣራ ይሆናል እንጂ።ዘፍ17፥15



ዘሩንም እንደ ምድር አሸዋ  እንደሚያበዛው ቃል ገባለት ።የአብርሐም ሚስት ሣራ ልጅ አልወለደችም ነበር በሚስቱ በሣራ ፈቃድ አብርሐም ከግብፃዊቷ  ከገረዱ ከአጋር እስማኤልን ወለደ ዘፍ16፥4። ቃል ኪዳንና  ምልክት ይሆነው ዘንድ ግዝረትን



አዘዘው።ከተወለደ ስምንት ቀን  ሲሆነው ወንድ ልጅ ይገረዝ፤ወንድ ሁሉ በትውልዳችሁ ይገረዝ።ቃል ኪዳኔም በሥጋችሁ የዘላለም ቃል ኪዳን ይሆናል። ዘፍ17፥12-14

አብርሐም እንግዳ ተቀባይና የሣራ የሚስቱ ታዛዥ ሰው ነበር።አብርሐምና ሣራ በእድሜያቸው ያረጁና በበረከት የተሞሉ ሰዎች ነበሩ። የሚኖሩትም በድንኳን ውስጥ ነበር።ሁለቱም እግዚአብሔርን የሚወዱና በእውነት የሚያመልኩ ሰዎች ነበሩ ። እንዲሁም በእንግዳ ተቀባይነታቸው እና አክባሪነታቸው የሚታወቁ ሰዎች ነበሩ ።



# አብርሐም /ክፍል2/

አብርሐም እንግዳ ከመውደዱ የተነሳ እንግዳ ካልመጣ ምግብ አይበላም ነበር። በዚህ መልካም ሥራው የቀናው ሰይጣን በሰው መልክ ተገልጦ ራሱን ገምሶ  ደሙን አፍስሶ  ወደ አብርሐም ቤት ወደሚወስደው መንትያ መንግገድ   ላይ ተኝቶ ወደ  አብርሐም ቤት የሚሄዱትን እንግዶች ሁሉ እንዲህ ብሎ ነገራቸው  የዱሮው አብርሐም አይምሰላችሁ  እኔም እንደ ድሮው መስሎኝ እቤቱ ብሄድ  እንዲህ ደሜን አፍስሶ ለቀቀኝ በእኔ የደረሠ አይድረስባችሁ እያለ ወደ አብርሐም ቤት እንዳይሄዱ ከለከላቸው ወይንም አስፈራራቸው።ድሮ አብርሐምን የሚጎበኙት  ወዳጆቹ  ሁሉ እቤቱ ከሄዱ ደማቸው ስለሚፈስ እና ስለፈሩ ቀሩ። አብርሐምም የሰይጣንን ተንኮል ሳያውቅ ሦስት ቀን ሙሉ ምንም ምግብ ሳይበላ እየተራበ ጠበቀ።በሦስተኛው ቀን አብርሐም ከድንኳን ደጃፍ ባለችው  ዛፍ ሥር ተቀምጦ ሳለ በሰይጣም ተንኮል ያልተሸነፈውን  አብርሐምን   ያየ እግዚአብሔር  የሠይጣንን ተንኮል ሊሽር ለአብርሐም ደግሞ በረከትን ሊሰጥ በመምሬ ዛፍ ሥር በሦስትነቱ ተገለጠለት።

ዓይኑንም አነሣና እነሆ፥ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ፤ ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ሮጠ፥ ወደ ምድርም ሰገደ፥ እንዲህም አለ። አቤቱ፥ በፊትህስ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ ባሪያህን  አትለፈኝ ብዬ እለምናለሁ፤ጥቂት ውኃ ይምጣላችሁ፥እግራችሁን ታጠቡ፥ ከዚህችም ዛፍ በታች ዕረፉ፤ ቍራሽ እንጀራም ላምጣላችሁ፥ ልባችሁንም ደግፉ  ከዚያም በኋላ ትሄዳላችሁ፤ ስለዚህ ወደ ባሪያችሁ መጥታችኋልና።

እነርሱም  እንዳልህ አድርግ አሉት።አብርሃምም ወደ ድንኳን ወደ ሣራ ዘንድ ፈጥኖ ገባና  ሦስት መስፈሪያ የተሰለቀ ዱቄት ፈጥነሽ አዘጋጂ፥ ለውሺውም፥ እንጎቻም  አድርጊ አላት። አብርሃምም ወደ ላሞቹ ሮጠ፥ እጅግ የሰባም ታናሽ ጥጃ ያዘና ለብላቴናው ሰጠው፥ያዘጋጅም ዘንድ ተቻኰለ።እርጎና ወተትም ያዘጋጀውንም ጥጃ አመጣ፥ በፊታቸውም አቀረበው፤ እርሱም ከዛፉ በታች በፊታቸው ቆሞ ነበር፥ እነርሱም በሉ።

እነርሱም  ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት? አሉት። እርሱም  በድንኳኑ ውስጥ ናት አላቸው።እርሱም   የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ በእውነት እመለሳለሁ፤ ሚስትህ ሣራም ልጅን ታገኛለች አለ። ሣራም በድንኳን ደጃፍ በስተ ኋላው ሳለች ይህንን ሰማች።አብርሃምና ሣራም በዕድሜአቸው ሸምግለው ፈጽመው አርጅተው ነበር፤ በሴቶች የሚሆነውም   ልማድ ከሣራ ተቋርጦ ነበር። ሣራም በልብዋ እንዲህ ስትል ሳቀች። ካረጀሁ በኋላ በእውኑ ልጅ አውልዳለሁን ? ጌታዬም ፈጽሞ ሸምግሎአል።እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው። ካረጀሁ በኋላ በውኑ እወልዳለሁን? ስትል ሣራ ለምን ሳቀች? በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን? የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ እመለሳለሁ፤ ሣራም ልጅን ታገኛለች።  ሣራም ስለ ፈራች። አልሳቅሁም ስትል ካደች። እርሱም አይደለም፥ ሳቅሽ እንጂ አላት። ሰዎቹም ከዚያ ተነሥተው ወደ ሰዶም አቀኑ፤ አብርሃምም ሊሸኛቸው አብሮአቸው ሄደ።

## ልናውቀው የሚገባ

ሥላሴ የሚለው ቃል ሠለሰ ሦስት አደረገ ካለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ሦስትነት ማለት ነው። ቅድስትሥላሴ ማለት ልዩ ሦስትነት ማለት ነው።

ልዩ ሦስትነት : ሦስት ሲሆን አንድ፣ አንድ ሲሆኑ ሦስት (ልዩ ሦስትነትን ማመንን ፈጽምልን (ጸሎተ ቡራኬ))

የክርስትና ዶግማ (መሠረተ እምነት) በምስጢረ ሥላሴ ላይ የተመሠረተ ነው። ለመዳናችንም መሠረት ነው።

## ባህርይና አካላት

አንድነት በባሕርይ፣ በመለኮት (በአምላክነት)፣ በሕልውና፣ በፈቃድ፣ በፈጣሪነት፣በአገዛዝ፣ በሥልጣን
(ዘዳ 6፥4 ኢሳ 44፥6 ኢሳ 43፥1 ዮሐ 10፥30)

ሦስትነት በግብር፣ በአካል፣ በስም፣ (ማቴ 28፥19 1ኛ ቆሮ 12፥4-6 ሮሜ 14፥17



## በግብር ሦስትነቱ

አብ : ወላዲ (አባት)፣ አሥራፂ አይወለድም፣ አይሰርፅም
ወልድ : ተወላዲ (ልጅ) አይወልድም፣ አያሰርፅም፣ አይሰርጽም
መንፈስ ቅዱስ : ሠራፂ (የሠረፀ) አይወለድም፣ አይወልድም፣ አያሰርፅም

## የአካል ሦስትነት

ለአብ ፍጹም አካል፣ ፍጹም መልክ፣ ፍጹም ገጽ አለው።
ለወልድም ፍጹም አካል፣ ፍጹም መልክ፣ ፍጹም ገጽ አለው ።
ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል፣ ፍጹም መልክ፣ ፍጹም ገጽ አለው።

## የስም ሦስትነት

አይከፋፈሉም፣ አይነጣጠሉም፣ ፍጹም አንድ ናቸው።
አብ፡ አባት፣ ልብ፣ /ከእኛ በላይ ያለው/ አምላክ
ወልድ፡ ልጅ (የባሕርይ)፣ ቃል፣ /ከእኛ ጋር ያለው/ አምላክ፣ የእግዚአብሔር ክንዱ፣ የአብ ቀኝ እጅ
መንፈስ ቅዱስ፡ እስትንፋስ፣ /በውስጣችን ያለው/ አምላክ፣ የአብ ምክሩ

# አብርሃም (ክፍል3 )

## የአብርሐም ፈተና

እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው ሣራን አሰበ፤ ሣራም ፀነሰች፥ እግዚአብሔርም በተናገረው ወራት ለአብርሃም በእርጅናው ወንድ ልጅን ወለደችለት። አብርሃምም የተወለደለትን የልጁን ስም ይስሐቅ ብሎ ጠራው። አብርሃምም ልጁን ይስሐቅን እግዚአብሔር እንዳዘዘው በስምንተኛ ቀን ገረዘው። አብርሃምም ልጁ ይስሐቅ በተወለደለት ጊዜ የመቶ ዓመት ዕድሜ ነበረ።

ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፥ እንዲህም አለው። አብርሃም ሆይ የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ፤ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለ።አብርሃምም የመሥዋዕቱን እንጨት አንሥቶ ለልጁ ለይስሐቅ አሸከመው፤ እርሱም እሳቱንና ቢላዋውን በእጁ ያዘ፥ ሁለቱም አብረው ሄዱ።ይስሐቅም አባቱን አብርሃምን ተናገረው። አባቴ ሆይ እሳቱና እንጨቱ ይኸው አለ፤ የመሥዋዕቱ በግ ግን ወዴት ነው? አለ።አብርሃምም ልጄ ሆይ፥ የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል አለው፤ ሁለቱም አብረው ሄዱ። እግዚአብሔር ወዳለውም ቦታ ደረሱ፤ አብርሃምም በዚያ መሠዊያውን ሠራ፥ እንጨትንም ረበረበ፤ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ በመሠዊያው በእንጨቱ ላይ አጋደመው።አብርሃምም እጁን ዘረጋ፥ ልጁንም ያርድ ዘንድ ቢላዋ አነሣ።


## በይስሐቅ ፋንታ በግ ተሰዋ

የእግዚአብሔር መልአክም ከሰማይ ጠራና። አብርሃም አብርሃም አለው፤ በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ፥ አንዳችም አታድርግበት፤ አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ ሆንህ አሁን አውቄአለሁ አለ። አብርሃምም ዓይኑን አነሣ፥ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ፤ አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፥ በልጁም ፋንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው።





እግዚአብሔር ይህን ነገር አድርገሃልና፥ አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፥ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ፤ ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል፤የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፥ ቃሌን ሰምተሃልና።



## አብርሃም ለይስሐቅ ሚስት እንደፈለገለት

እኔም አብሬ ከምኖራቸው ከከነዓን ሴቶች ልጆች ለልጄ ሚስት እንዳትወስድለት በሰማይና በምድር አምላክ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ፤ ነገር ግን ወደ አገሬና ወደ ተወላጆቼ ትሄዳለህ፥ ለልጄ ለይስሐቅም ሚስትን ትወስድለታለህ። ርብቃ የአብርሃም ወንድም የናኮር ልጅ ናት። ሎሌውም የከበረ ስጦታንም ለወንድምዋ ለላባና ለእናትዋአቀረበ።ርብቃንም ለይስሐቅ ሚስት ትሆነው ዘንድ ወሰደለት፥ይስሐቅም ወደ እናቱ ወደ ሣራ ድንኳን አገባት፥ ርብቃንም ወሰዳት፥ ሚስትም ሆነችው፥ ወደዳትም፤ ይስሐቅም ከእናቱ ሞት ተጽናና።



ርብቃም መጀመሪያ መካን ነበረች ። ባልዋ ከጸለየላት በኋላ ግንጸነሰች በሆድዋም ውስጥ መንታ ልጆች ይገፋፉ ነበር። እርግዝናው ስለጸናባት ወደ እግዚእብሔር ጸለየች እርግዝናው ስለጸናባት እግዚአብሔርን በጸሎት ጠየቀች። እግዚአብሔርም ታላቁ ለታናሹ እንደሚገዛ ነገራት ።ያዕቆብና ኤሳውን ወለደች።



ወትቀውም ንግሥት በየማንከ
በአልባሰ ወርቅ ዑጽፍት ወሑብርት።
ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአፅምዒ እዝነኪ
መዝ.44፥11

በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና
ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች።
ልጄ ሆይ፥ ስሚ እዩ ጆሮሽንም አዘንብዪ፤

# እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ትውልዷ በአባቷ በኩል ከንጉሡ ከዳዊት ወገን ነው፤ በእናቷም በኩል ከካህኑ ከአሮን ወገን ነው፤ የአባቷ ስም ኢያቄም ነው፤ የእናቷም ስም ሐና ነው፡፡

ቅዱስ ኢያቄም እና ቅድስት ሃና መካን ነበሩ /ልጅም አልነበራቸውም/ ፥ በእርጅናቸው ዘመን በስዕለት እመቤታችን ድንግል ማርያምን ግንቦት 1 ቀን ወለዱ። እግዚአብሔር አምላክ ልጅ ከሰጠኸን ልጃችን የቤተ መቅደስ አገልጋይ ይሆናል ብለው ስለተሳሉ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልክ 3 ዓመት ሲሆናት ታህሳስ 3 ቀን ወደ ቤተ መቅደስ ገባች (ይህም ቀን በዓታ ለማርያም ተብሎ በቤክርስቲያናችን ይከበራል) ።



እቤተመቅደስ ስትገባ ምግቧንና መጠጧን (የሚሰጣት) የሚያዘጋጅላት ከእግዚአብሔር የተላከው መልአኩ ፋኑኤል ነበር።እመቤታችን በቤተ መቅደስ ስትኖር ሐርና ወርቅ እያስማማች ፥እየፈተለች ፥ ቤተመቅደስ እያገለገለች አደገች።

ለአቅመ አዳም ስትደርስ ለቅዱስ ዮሴፍ እጮኛ ትሆነው ዘንድ ተሰጠች።ይህም ማለት ቅዱስ ዮሴፍ እንዲጠብቃት፥እንዲያገለግላት ነው እንጂ እርሱ ሚስት አስፈልጎት አይደለም ። በእድሜው በጣም ያረጀ ሰውና ጻድቅ ስለሆነ።



እመቤታችን ለዮሴፍ ከታጨች በኋላ መላእኩ ቅዱስ ገብርኤል ሊያበሥራት ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ መጣ እንዲህም አላት „ጸጋን የተመላሽ ድንግል ሆይ ሰላም ላንቺ ይሁን አንቺ ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ (ሉቃ.1፥28 )፥ እነሆ ትጸንሻለሽ፥ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ „ብሎ አበሠራት ። እመቤታችን ድንግል ማርያምም „ወንድ ሳልውቅ ይህ እንዴት ይሆናል „ብላ መልአኩን ጠየቀችው መልአኩም „መንፈስ ቅዱስ የጸልልሻል ፥ የልዑል ኃይል ይጋርድሻል ፥ይህ የሚወለደውም ልዑል የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል ብሎ አበሠራት ።እሺ „እንደቃልህ ይደረግልኝ ብላ ለመልአኩ መለሰችለት“።



ከዚያ በኋላ እመቤታችን ዘመድዋ ኤልሳቤጥን /አክስትዋ/ ለመጠየቅ ወደ ተራራማው የኤፍሬም ሐገር ሄደች ። ኤልሳቤት እመቤታችን ድንግል ማርያምን ባየቻት ጊዜ „የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል „ አለቻት። ኤልሳቤጥ የስድስት ወር ነፍሰጡር ነበረች። ጽንሱ የእመቤትችንን ድምጽ ሲሰማ በኤልሳቤጥ ሆድ ውስጥ ዘለለ /ሰገደ/ ጽንሱም ዮሐንስ መጥምቅ ነበረ።





ልጅህን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለ ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ ካይልም
ምሳሌ 22፥6

# ሰብአ ሰገል (የጥበብ ሰዎች)



እግዚአብሔር ለአዳም በአምስት ቀን ተኩል ከልጅ ልጅህ ተወልጄ በመስቀል ተሰቅዬ በሞቴ አድንንለሁ ብሎ ቃል ገብቶለት ነበር መጽሐፈ ቀለሜንጦስ፡፡ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ሲወለድ ሰብአ ሰገል ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ ። ሰብአ ሰገል /ሦስቱ ነገሥታት *የጥበብ ሰዎች*/ ማንቱሲማር፣ በዲዳስፋ እና ሜልኩ የተባሉ የመጡት በኮከብ እየተመሩ ነበር።ኮከቡ የሚታየው ለነርሱ ብቻ ነበር ከተማ ሲገቡ አይታይም ነበር ፡፡ ማንኛውም ኮከብ ሌሊት እንጂ በቀን አይታይም ይህ ይኽ ኮከብ ግን ቀን ቀን ይታያቸው ነበር ፥ የጥበብ ሰዎቹን በቀን ና በሌሊት እየመራ ቤተልሔም ውስጥ አድርሷቸዋል::።

ኢየሩሳሌም ከተማ ሲደርሱ ኢንዲህ ሲሉ ጠየቁ ኮከቡን በምሥራቅ ዓይተን እንሰግድለት ዘንድ መጥተናልና ፥የተወለደው ንጉሥ ወዴት ነው ? ብለው ። ሰብዓ ሰገል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም እንደሚወለድ እንጂ በየት ሥፍራ እንደሚወለድ አያውቁም ነበር። ሄሮድስ ይኸን ቃል ሲሰማ እጅግ በመደናገጡና የኢየሱስ ክርስቶስም መወለድ ለሥልጣኑ እንደሚያሳስበው በመገመት ሰብአ ሰገልን በስውር ጠርቶ ሕፃኑን ባገኛችሁት ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ በማለት ሌላ ንጉሥ የመጣ ስለመሰለው በሚሰጥር ሊገድለው አስቦ በሽንገላ አነጋገር ተናገራቸው ። ሆኖም ግን ሰብዓ ሰገል ከኢየሩሳሌም እንደወጡ በምሥራቅ ያዩት ኮከብ እየመራ ጌታችን እስከተወለደበት ስፍራ (ቤተልሔም) ድረስ አድርሷቸው ቆመ ። የተወለደበት ቦታ ሲደርሱም በጣምም ደስ አላቸው ። ህፃኑን ኢየሱስን ከእናቱ ጋር አገኙ ወድቀውም ሰገዱለት ሳጥናቸውንም ከፍተው ስጦታችውን (እጅ መንሻ አቀረቡለት) ወርቅና ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት ::

ዕጣን:- የተበረከተለት አንተ ያልተፈጠርክ ኋላም የማታልፍ አምላክ ነህ ሲሉ::

ከርቤ:- ያቀረቡለት አንተ የማትሞት ስትሆን ግን መራራ ሞትን ትቀበላለህ ሲሉ::

ወርቅ:- ያቀረቡለት አንተ የዓለሙ ሁሉ ገዥ ንጉሥ ነህ ሲሉ::

ጌችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ በ፵ኛው ቀን ወደ ቤተ መቅደስ በመግባት የኦሪትን ሕግ ፈጽሟል ::

ሽማግሌው ስምዖን በጣም እረጅም ዓመት (ለሦስት መቶ ዓመታት) የጌታን መወለድ ከእግዚአብሔር ተነግሮት በቤተ መቅደሰ ሆኖ ሲጠባበቅ ነበር። በቅዱስ ወንጌል እንደ ተጻፈ በስምንተኛው ቀን እንደ ኦሪቱ ሥርዓት ግዝረት ይፈጸምለት ዘንድ ፥ ሕፃኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ቤተ መቅደስ ወሰዱት ። ይህም ቀን ጥር ፮ ሲሆን በዓለ ግዝረት ይባላል።ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ሰብአ ሰገል የሄሮድስን ትእዛዝ ሰምተው ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይመለሱ ሦስቱም አንድ ዓይነት ኅልም ማየታቸው ነው ። በኮከብ እየተመሩ ጌታ ከተወለደበት የደረሱት የጥበብ ሰዎች በሕልም ከእግዚአብሔር ተነግሯቸው ደግሞ በሌላ አቅጣጫ ወደ መጡበት ስፍራ ተመልሰዋል።ሰብአ ሰገል ከሄዱ በኋላ መልአክ ዮሴፍን ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ፥ ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ (ወደ ግብፅ ተሰደዱ)፥ እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው። እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን በሌሊት ያዘና ከጌታ ዘንድ በነቢይ። ልጄን ከግብፅ ጠራሁት የተባለው እንዲፈጸም ወደ ግብፅ ሄደ፥ ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ በዚያ ኖረ።ማቴ.፪፡፲፫-፲፭ ከዚህም በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገል እንደ ተዘባበቱበት ባየ ጊዜ እጅግ ተቈጣና ጭፍራዎቹን ልኮ ከሰብአ ሰገል እንደ ተረዳው ዘመን ልክ ሁለት ዓመት የሆናቸውንና፥ከዚያም የሚያንሱትን፥ በቤተ ልሔምና በአውራጃዎችዋ ሁሉ የነበሩትን ሕፃናት ፥ንጉሥ ይሆናል የተባልው ህጻን ይኖራል በማለት (ሄሮድስ ጌታችንን ያገኘ መስሎት) 144 ሺህ የቤቴልሔም ሕፃናትን አስገደለ።

ቃላት

ሰብአ ሰገል የግእዝ ቃል ነው= ሰብአ ማለት ሰው ሲሆን ሰገል ደግሞ ጥበብ ማለት ነው

በስውር ጠርቶ =በድብቅ አስጠርቶ

በሽንገላ አነጋገር =በውሸት (በማታለል)አነጋገር

እጅ መንሻ =የሚሰጥ ስጦታ

እጅ ነሳ =ከወገብ ጎንበስ ብሎ አከበረ

ጭፍራዎቹን =ወታደሮቹን

የማታልፍ =የማትሞት (ህይወቱ አለፍች =ሞተ)

በሌላ አቅጣጫ =በሌላ መንገድ

ሽሽ =አመለጠ፥ ተሰደደ

ተዘባበቱበት=ደዋሹት





# ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ (ክፍል 1)

በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበረ፤ ሚስቱም ስምዋም ኤልሳቤጥ ነበረ።ሁለቱም የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ። ኤልሳቤጥም መካን ነበረችና ልጅ አልነበራቸውም፤ ሁለቱም በዕድሜያቸው አርጅተው ነበር።

በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል፥እንደ ካህናት ሥርዓት ወደ እግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ገብቶ ለማጠን ዕጣ ደረሰበት።በዕጣንም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር። የጌታም መልአክ በዕጣኑ መሠዊያ ቀኝ ቆሞ ታየው። ዘካርያስም ባየው ጊዜ ደነገጠ፥ ፍርሃትም ወደቀበት። መልአኩም እንዲህ አለው። „ዘካርያስ ሆይ፥ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፥ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ።ደስታና ተድላም ይሆንልሃል፥ በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል።“

ዘካርያስም መልአኩን። እኔ ሽማግሌ ነኝ ሚስቴ በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን አውቃለሁ? አለው። መልአኩም መልሶ። „ እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፥ እንድናገርህም ይህችንም የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር፤እነሆም፥ በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ፥ ይህ ነገር እስከሚሆን ቀን ድረስ ዲዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም አለው።“

ሕዝቡም ዘካርያስን ይጠብቁት ነበር፤ በቤተ መቅደስም ውስጥ ስለ ዘገየ ይደነቁ ነበር።በወጣም ጊዜ ሊነግራቸው አልቻለም፥ በቤተ መቅደስም ራእይ እንዳየ አስተዋሉ፤ እርሱም ይጠቅሳቸው ነበር፤ ድዳም ሆኖ ኖረ።

የማገልገሉም ወራት ሲፈጸም ወደ ቤቱ ሄደ ሚስቱም ኤልሳቤጥ ፀነሰች። ሕፃኑም ተወለደ ፥ የመልአኩን የብሥራት ቃል ባለመቀበሉ አንደበቱ ተይዞ የነበረው ካህኑ ዘካርያም ስሙ „ዮሐንስ“ ይባል ብሎ ሲጽፍ አፉ ተከፈተ፤ አንደበቱም ተፈታና ፥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንደዚህ አለ፡-„ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ፥ የልዑል ነቢይ ትባላለህ፥ መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህና፤ እንደዚህም የኃጢአታቸው ስርየት የሆነውን የመዳን እውቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ፤ ይህም ከላይ የመጣ ብርሃን በጐበኘበት በአምላካችን ምሕረትና ርኅራኄ ምክንያት ነው፤ ብርሃኑም በጨለማና በሞት ጥላ ተቀምጠው ላሉት ያበራል እግሮቻችንንም በሰላም መንገድ ያቀናል።“ (ሉቃ ፩፥፸፯-፸፱ በዚያም ዘመን ሄሮድስ የአምላካችን፣ የጌታችንና የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መወለድ ከሰብአ ሰገል ሲሰማ መንግሥቴን ይወስድብኛል ብሎ በመፍራቱ የቤተልሔም ሕፃናትን መግደል የመጀመርያ ውሳኔው ሆነ። (ማቴ. ፪፥፩-፲፯) የሄሮድስ ጭፍሮችም የተወለደውን ህፃን ዮሐንስን ፈልገው ባጡት ጊዜ አባቱን ዘካርያስን በቤተ መቅደስ ውስጥ በሰይፍ ገደሉት፤ ካህናቱም በንጹሕ ልብስ ገንዘው በአባቱ በበራክዩ መቃብር ቀበሩት፡፡ ቅድስት ኤልሳቤጥም ልጇን ዮሐንስን (እንዳይገድሉባት) ይዛ ወደ ምድረ በዳ(በገዳመ ዚፋታ) ተሰደደች በዚያም አደገ። ቅድስት ኤልሳቤጥ ወደ በረሃ በገባች በአምስተኛ ዓመቷ፤ ቅዱስ ዮሐንስም ሰባት ዓመት ሲሞላው ሕፃኑን ከዚህ ዓለም ተለየች (ሞተች)፡፡ ቅዱስ ዮሐንስም እግዚአብሔር ከአራዊት አፍ እየጠበቀው፤ ሲርበው ሰማያዊ ኅብስትን እየመገበው ሲጠማውም ውኃ እያፈለቀ እያጠጣው፤ አናብስቱና አናምርቱ እንደ ወንድምና እኅት ኾነውለት በበረሃ መኖር ጀመረ፡፡ በበረሃ ሲኖርም የግመል ጠጉር ይለብስ፣ በወገቡም ጠፍር ይታጠቅ፣ አንበጣ እና ማር ይመገብ ነበር (ኢሳ.፵፥፫-፭)።የአዋጅ ነጋሪው ቃል ተብሎ የተነገረለት ቅዱስ ዮሐንስ ጊዜው ሲደርስ ከነበረበት በረሐ ድምፁን እያሰማ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ! እያለ እየሰበከ በዮርዳኖስ ዙሪያ ወዳለው አገር ሁሉ ወጣ። (ሉቃ. ፫፥፫-፮) ። በነቢዩ በኢሳይያስ „የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ“ (ኢሳ ፵፥፫) እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ የተባለለት ይህ ነውና።

## ቃላት

ዮሐንስ ማለት= *እግዚአብሔር ጸጋ ነው* ማለት ነው (ተድላና ደስታ)
በረሐ = ምድረ በዳ (ውኃ ዛፍ የሌለበት ሞቃታማ ቦታ) በግእዝ ገዳም ማለት ነው
አዋጅ= የሚነገር ማስታወቂያ
ያለ ነቀፋ=ያለ ጥፋት ፥ያለ እንከን
ኤልሳቤጥም መካን ነበረች = ልጅ መውለድ እትችልም
ተድላ = ደስታ
ዲዳ =መናገር የማይችል
አንደበቱም ተፈታና =መናገር ቻለ
ራእይ እንዳየ አስተዋሉ =ወደፊት የሚሆነውን አወቀ
አራዊት=የዱር አውሬ( ለምሳሌ አንበሳ ፥ነብር)
በሰይፍ ገደሉት=በትልቅ ጎራዴ ገደሉት
በንጹሕ ልብስ ገንዘው =በንጹህ ልብስ ሸፍነው
ውኃ እያፈለቀ=ውኃ ከመሬት እያወጣ
አናብስቱና አናምርቱ=የአንበሳ የነብር ብዙ
ጠፍር =ከቆዳ የተሰራ( ለምሳሌ ቀበቶ)
ንስሐ ግቡ! = ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ
ዘገየ =ቆየ
ይጠቅሳቸው ነበር= በእጁ ያሳያቸው ነበር

## ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ (ክፍል 2)

ዮሐንስ ንጉሡን ሳይፈራ ከአምላኩ የሕይወትን አክሊል ከሰጪው እግዚአብሔር ሊቀበል እውነትን ሰበከ፤ እውነትን አስተማረ። እንዲህም ሲልም ጮኸ፤ “ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ „ብሎ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ። በነቢዩ በኢሳይያስ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ የተባለለት ይህ ነውና ። ዮሐንስ የግመል ጠጉር ልብስ ነበረው፥ በወገቡም ጠፍር ይታጠቅ ነበር፤ ምግቡም አንበጣና የበረሀ ማር ነበረ።” ማቴ.፫፡፩-፬ /ማቴ.3፡1-4/ /ማር.፩፡፩-፮ /ማር.1፡1-6/ ዮሐ.፩፡፳፫ /1፡23/“ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለ። የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ እኔ ነኝ አለ።” ዮሐ.፩፡፳፫ /1፡23/

ዮሐንስ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ሊያድን እንደመጣ ይገልጽ ነበር ።በዮርዳኖስ ወንዝም በውኃ ያጠምቅ ነበር ። ጥምቀቱም የንስሐ ነበር።ጌታችንም ወደ ዮሐንስ ሊጠምቅ ሄደ ። ዮሐንስ ግን እኔ በአንተ ልጠመቅ ይገባል ብሎ እምቢ አለ። ኢየሱስም እንግዲህ ጽድቅን ሁሉ ልንፈጽም ይገባልና አለው። ኢየሱስም በዮርዳኖስ ከተጠመቀ በኋላ ሰማይ ተከፈተ እግዚአብሔር አብ ከሰማይ ሆኖ በርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት አለመንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በጌታ ላይ ተቀመጠ። ዮርዳንዕስ ባህር የሥላሴ መገለጥ ሆነ ።ይህም ቀን በቤተክርስቲያናችን ጥምቀት በመባል ጥር 11 በደማቅ ሁኔታ በየዓመቱ ታቦታቱ በወንዝ ዳር እያደሩ ይከበራል

በዚያን ዘመን ንጉስ ሄሮድስ የወንድሙን ሚስት ሄሮድያዳን አግብቶ ነበር። በዚህም ምክንያት የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት ማግባት እንደሌለበት „የወንድምህ ሚስት ለአንተ ልትሆን አልተፈቀደም



ይለው ነበርና።“ ሄሮድስም እኔን ንጉሡን እንዴት ይገስጻኛል በማለት አሰረው። ሄሮድያዳ ግን ዮሐንስን ልትገድለው ብትፈልግም አልቻለችም። ሄሮድስ ዮሐንስ ጻድቅና ቅዱስ ሰው እንደ ሆነ አውቆ ይፈራውና ይጠባበቀው ነበር፤ እርሱንም ሰምቶ በብዙ ነገር ያመነታ ነበር፤ በደስታም ይሰማው ነበር።

ሄሮድስም በተወለደበት ቀን ለመኳንንቱና ለሻለቆቹ ለገሊላም ሹማምንት ግብር ባደረገ ጊዜ ምቹ ቀን ሆነላትና የሄሮድያዳ ልጅ ገብታ ስትዘፍን ሄሮድስንና ከእርሱ ጋር የተቀመጡትን ደስ አሰኘቻቸው። ንጉሡም ብላቴናይቱን። የምትወጂውን ሁሉ ለምኚኝ እሰጥሽማለሁ አላት፤ የመንግሥቴ እኩሌታ እንኳ ቢሆን የምትለምኚውን ሁሉ እሰጥሻለሁ ብሎ ማለላት። ወጥታም ለእናትዋ። ምን ልለምነው? አለች። እርስዋም። የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ አለች። ወዲያውም ፈጥና ወደ ንጉሡ ገብታ። የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ በወጭት አሁን ልትሰጠኝ እወዳለሁ ብላ ለመነችው። ንጉሡም እጅግ አዝኖ ስለ መሐላው ከእርሱም ጋር ስለ ተቀመጡት ሊነሣት አልወደደም። ወዲያውም ንጉሡ አሽከሩን ልኮ ራሱን እንዲያመጣ አዘዘው። ሄዶም በወኅኒ ራሱን ቈረጠ፥ ራሱንም በወጭት አምጥቶ ለብላቴናይቱ ሰጣት፥ ብላቴናይቱም ለእናትዋ ሰጠች። ደቀ መዛሙርቱም ሰምተው መጡ በድኑንም ወስደው ቀበሩት መጥተውም ለኢየሱስ አወሩለት።(ማር.፮፤፲፯-፳፱ /6፡17-29/ ማቴ.፲፬፡፩-፲፫ /ማቴ.14፡1-13) ይህም መስከረም 2 ቀን በቤተክርስቲያናችን „ምትረተ ርእሱ ለዮሐነስ „ በመባል ይከበራል ወይንም በመላው ኢትዮጵያ ቅዱስ ዮሐንስ በመባል ከዘመን መለወጫ ጋር አብሮ ይከበራል።

## ዐቢይ ጾም

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ30 ዓመቱ በማየ ዮርዳኖስ በዕደ ዮሐንስ ከተጠመቀ በኋላ ሳይውል ሳያድር ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ሄደ፡፡በዚያም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመ፡፡ይህም ጌታችን የጾመው ጾም ልዩ ልዩ መጠሪያዎች አሉት። እንደ ነቢያት ስርዓት አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ስለጾመ ጾመ **አርብዓ (አርባ ጾም)** ይባላል።ስሙ መድኅኒት የሆነ ጌታ የነፍስ ቁስል የሆኑ ሦስቱን ዐበይት ኃጢአቶች (ስስት፣ ትዕቢትና ፍቅረ ንዋይ) ድል ያደረገበት በመሆኑ **የድል ጾም፣ ጾመ ኢየሱስ** በመባል ይታወቃል፡፡ የፍጥረት ሁሉ ጌታ፣ ልዑለ ባሕርይ፣ ሰው የሆነ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው በመሆኑ ከሌሎች አጽዋማት ተለይቶ **ዐቢይ (ታላቅ፣ ዋና) ጾም** ይባላል፡፡ ለረዥም ጊዜ የሚጾም፣ ብዙ መንፈሳዊ በረከት የሚገኝበት ጾም በመሆኑ ብዙ ምርት ከሚያስገኝ ሰፊ እርሻ ጋር በማመሳሰል **ጾመ ሁዳዴ** ይባላል፡፡

አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያምበትም ጊዜ በሰይጣን ተፈተነ ። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተፈተነው እኛ በፈተና ጊዜ “አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን” ብለን እንድንጸልይ ሊያስተማረን፣ ወደ ፈተና በገባን

ጊዜም በቅዱስ ስሙ፣ በህያው ቃልኪዳኑ ተማምነን እንድንለምነው በዚህም በሕይወታችን መፈተን እንዳለብን አስተማረን፡፡ በክርስትና በሕይወታችን ብዙ ፈተናዎች አሉና፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስቱን ፈተናዎች በሦስት ቦታዎች ተፈተነ፡፡ አንዱን በገዳም፣ ሁለተኛውን በቤተመቅደስ፣ ሦስተኛውን ደግሞ በተራራ (በቤተመንግስት) ተፈተነ፡፡ ሦስቱን ዐበይት ኃጢአቶች

1/ ስስት፣ የመጀመሪያው ፈተና በዚያው በገዳመ ቆሮንቶስ ሲሆን ፈተናውም ስስት ነበር፡፡ ዲያብሎስ ሥጋን የተዋሐደውን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን ተርቦ ቢያየው ‹‹የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እነዚህ ድንጋዮች ዳቦ እንዲሆኑ እዘዝ›› በማለት ፈትኖታል፡፡

በስስት የመጣውን በትዕግስት ድል ነሳው፡፡ ‹‹ይህንን ድንጋይ ዳቦ አድርግ›› በማለት የመጣውን ፈተና ‹‹ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም፣ በእግዚአብሔር ቃል እንጂ›› ብሎ መለሰለት (ዘዳ 8፡3)፡፡

2/ ትዕቢትና ሁለተኛው ፈተና ደግሞ በቤተመቅደስ ሲሆን ፈተናውም ትዕቢት ነበር፡፡ ‹‹መላእክት ያነሱኃል ተብሎ ተጽፏልና ራስህን ከመቅደስ ጫፍ ወርውር›› (መዝ 90፡11) ይህ ፈተና ከመጻሕፍት ጥቅስ ጠቅሶ የፈተነበት ነው፡፡

በትዕቢት የመጣውን ፈተና ደግሞ በትህትና ድል ነሳው፡፡ ‹‹መላእክቱ በእጃቸው ያነሱሃል›› ተብሎ ተጽፏልና ራስህን ወርውር ቢለው ‹‹ጌታ አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተጽፏልና›› (ዘዳ 6፡16) በማለት አሳፈረው፡፡

3/ ፍቅረ ንዋይ ሦስተኛው ፈተና ደግሞ በተራራ ጫፍ (በሰገነት) ሲሆን ፈተናውም የፍቅረ ንዋይ ነበር፡፡ ‹‹ወድቀህ ብትሰግድልኝ የዓለምን መንግስታት ክብራቸውንም ሁሉ እሰጥሀለሁ›› በማለት ፈትኖታል፡፡

በፍቅረ ንዋይ የመጣውን በጸሊዐ ንዋይ ድል ነሳው፡፡ ‹‹ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏልና›› (ዘዳ 6፡13) በማለት መልሶታል፡፡ ነገስታት/ባለስልጣናት ቤታቸውን በከፍታ/በሰገነት ሠርተው ለህብትና ለሥልጣን ሲሮጡ በባዕድ አምልኮ ይፈተናሉና ይህንን ድል መንሻ ሠራላቸው፡፡

ጾመ ሁዳዴ ይህ ጾም በቤተክርስቲያናችን ካሉት 7 አጽዋማት አንዱና ትልቁ ጾም ነው